## የባህር ውስጥ ኑሮ

የምንማርባቸው ትምህርት ቤቶች፣ የምንጫወትባቸው ፓርኮች፣ የምንተነፍሰው አየር፣ ከላያችን ያለው ሰማይ፣ ጫፍ ያላቸው ተራሮች፣ የሚጎርፉ ወንዞች እነዚህ ሁሉ በዓለማችን ላይ የሚገኙ ነገሮች ናቸው፡፡

ከኛ ውጪ ሌሎች አካላትም በመሬት ላይ ይኖራሉ፡፡

ወፎች፣ የሜዳ አህዮች፣ ዝሆኖች፣ ቀጭኔዎች፣ ድመቶች…

ዛፎች፣ አበቦች፣ ፍራፍሬዎች፣ አትክልቶች…

ሆኖም እነዚህ እፅዋት እና እንስሳት እንዲሁም እኛ ልንኖር የማንችልበት ሌላ አለም አለ፡፡

ይህ ከውሀ በታች ያለው አለም ነው፡፡

እዚህ የሚኖሩ ፍጥረታትም አሉ፡፡

በቡድን የሚጓዙት የክላውን አሳዎች፣ መርዛማ እሾክ ያለው ጊንጥ አሳ፣ ልክ እንደ ተወዛዋዥ የሚሄደው ጠፍጣፋ ትል፡፡ ኮከብ አሳ እና ሌሎች በርካታ ነገሮችን አላህ በባህር ውስጥ ያኖራል…

አለማችን ምን እንደምትመስል አያውቁም፡፡

አላህ በባህር እና በውቀያኖሶች ውስጥ ለመኖር በሚያመች መልኩ ፈጥሮአቸዋል፡፡

አሁን አጭር ጉዞ በማድረግ በባህር ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረታትን እንወቅ፡፡

## ኮራል ፓሊኘስ

እኛ ኮራል ፓሊኘሶች ነን….

እፅዋት ናቸው ብላችሁ ልትገምቱ ትችላላችሁ ሆኖም እኛ እንስሳት ነን፡፡

የሚያልፈውን ምግብ ይዘን እንመገባለን፡፡

በሰውነታችን ውስጥ ለሚገኘው ኬሚካላዊ ንጥረ ነገር ምስጋና ይግባው ከጠላቶቻችን ተጠብቀናል፡፡

በትኩረት እኛን ተመልከቱ…

እነዚህን ኮራሎች የሰራን ትናንሽ ሠራተኞች ነን፡፡

## አፅጂው አሳ

እነዚህ አሳዎች ምን እያደረጉ ይመስላችኋል?

ሌሎች አሳዎች እንዲያፀዷቸው በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

እነዚህን የመሰሉ ትላልቅ አሳዎች እራሳቸውን ለማፅዳት ሌሎች ከእነሱ የሚያንሱ አሳዎች ያስፈልጓቸዋል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ትናንሽ አሳዎች ጥገኛ ትላትሎችን ከጊሎቻቸው እንዲያፀዱላቸው ይፈቅዳሉ፡፡

ትናንሽ አሳዎችም አፎቻቸው ውስጥ ሳይቀር ያለምንም ፍርሀት በመግባት የአሳውን ጥርስ እና ጊል ያፀዳሉ፡፡

በተመሳሳይ ሰዓት እራሳቸውን ይመግባሉ፡፡ ትላልቅ አሳዎች የሚያፀዷቸውን አሳዎች ምንም ጉዳት አያስከትሉባቸውም፡፡

እንዴት አፅጂው አሳ ትልቁ አሳ እንደማይጎዳው አወቀ?

እንዴት ሊያምኗቸው ይችላሉ?

ትላልቅ አሳዎች እንደማይበሏቸው እንዴት እርግጠኛ ሊሆኑ ቻሉ?

በርግጥም አፅጂው አሳ እነዚህን አደጋዎች መተማመን አይችልም፡፡ ነገር ግን አላህ እነዚህን ሁለት አሳዎች እነዴት እርስ በርስ መጠቃቀም እንዳለባቸው አሳወቃቸው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በምሉዕ ሰላም እና ትብብር በአንድ ላይ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል፡፡

## ክላውን አሳ

እንዴት ናችሁ? እኛ ክላውን አሳዎች ነን…

እናንተ እንደምታውቋቸው ክላውኖች አይደለንም  አይደል?

ይህ የሆነው እኛ የባህር ክላውኖች ስለሆንን ነው…

የክላውን አሳዎች ደማቅ ከለር ሲኖራቸው "ሲአኒሞን" በመባል በሚታወቁ እፅዋት መሰል አካላት ላይ ይኖራሉ።

በሲአኒሞን ቅርንጫፍ ላይ የተጣበቁ ሽፋኖች ይገኛሉ። እናም የሚነካቸው ማንኛውም አሳ ይሞታል ወይም ከፍተኛ ጉዳት ይደርስበታል።

ነገር ግን ሲአኒሞኖች እኛ ላይ ምንም ጉዳት አያደርሱብንም።

በእነሱ ቅርንጫፍ በመደበቅ እራሳችንን እንጠብቃለን።

ከተጣባቂ ሽፋኖች መጠበቃችን እያስገረማችሁ ነው አይደል?

ሲአኒሞኖች ሊጎድዋቸው ያልቻሉበት ምክንናያት በሚያመርቱት ልዩ ንፋጥ አማካኝነት ነው።

ስለዚህ ነገር በጥልቅ እናስብ፡-አሳው በአካባቢው ከሚገኙ ተጣባቂ ሽፋኖች የሚጠብቀውን ልዩ ንጥረ ነገር በአካሉ ላይ ያመርታል።

አደጋ ወደ አካባቢው ሲጠጋ አሳው ምንም ጉዳት እንደማያደርሱበት ያወቀ ይመስል በነዚህ ተጣባቂ ሽፋኖች ውስጥ ይደበቃል።

ሌሎች አሳዎች እዚያ መኖር እንደማይችሉ እና ተመሳሳይ ንፍጥን ማመንጨት እንደማይችሉ እንዴት አወቀ?።

በርግጥም ለትንሽዬ አሳ ይህን ማወቅ እና እነዚህን ነገሮች መስራት የማይቻል ነገር ነው።

አላህ ነው ያሳወቀው።

አላህ ሁሉንም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ፈጥሮ በእነሱ ላይ ምን መስራት እንዳለባቸው የሚመራ እውቀትን አሳድሮባቸዋል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ኢንስቲንክት (የተጥሮ ስጦታ) ብለው የሚገልፁት አላህ (ሡ.ወ) ሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ያሳደረው ፀባይ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እኛን የሰው ልጆችንም ፈጥሯል…

በመፅሀፋችን በቁርአን አማካኝነት ምን መስራት እንዳለብን ነግሮናል፡፡ አላህ ይህን የቁርአን ገፅታ በሚከተው አንቀጽ ይጠቁመናል፡፡

***"ይህ ወደናንተ ያወረድነው ብሩክ መፅሀፍ ነው፡፡ አንቀፆቹን እንዲያስተነትኑ የአእምሮዎች ባለቤቶችም እንዲገሰፁ አወረድነው፡፡" (ሱራህ ሷድ፡29)***

## <u>የባህር ውስጥ ፈረስ</u>

ሄይ! እኛን መመልከት ትችላላችሁ?

ምነው መመልከት አልቻላችሁም?

በደንብ ተመልከቱ! እኛ የባህር ውስጥ ፈረሶች ነን፡፡

ከለራችን እና በአካላችን ላይ ያሉት ቅርንጫፎች አብረን ከምንኖራቸው ኮራሎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለዚያ ነው እኛን ማየት ያልቻላችሁት፡፡

ከኮራሎች ጋር እራሳችንን እናመሳስላለን፡፡ ይህም ለሌላ የባህር ውስጥ ፍጥረታት እኛን እና ልጆቻችንን ማየት እና ማደን የማይቻል አድርጎታል፡፡

አላህ የአንድ ሴንቲ ሜትር ቁመት ብቻ ያላቸውን እራሳቸውን በማመሳሰል ወይም ከካባቢያቸው ጋር በመመሳሰል እራሳቸውን በመደበቅ ከጠላቶቻቸው እይታ የሚተርፉ ፍጥረታትንም ፈጥሯል፡፡

## <u>የባህር ውሰጥ ኤሊ</u>

የባህር ውስጥ ኤሊዎች የመራቢያ ጊዜአቸው ሲደርስ ሁሉም ወደ ባህር ዳርቻው ያመራሉ፡፡

ነገር ግን ይህ ማንኛውም የባህርዳርቻ አይደለም። የተወለዱበት የባህርዳርቻ እንጂ… ወደተወለዱበት ስፍራ ለመመለስ አንዳንድ ጊዜ እስከ ስምንት መቶ ኪሎ ሜትሮች ወይም አምስት ማይሎችን መጓዝ አለባቸው።

በጉዞው መጨረሻ ላይ እንቁላላቸውን አሸዋ ውስጥ ይቀብሩታል።

ሁሉም በተመሳሳይ ባህርዳርቻ መገናኘት እንዴት እንደቻሉ ታውቃላችሁ?

ተመሳሳይ ነገርን በተለያዩ ሰአታት እና በተያዩ የባህር ዳርቻዎች ቢያደርጉ ምን ይፈጠራል? ትውልዶቻቸው በሕይወት መቆየት ይችላሉን?

ይህን ጉዳይ የሚያጠኑ ተመራማሪዎች እጅግ በጣም አስደናቂ ነገርን አግኝተዋል።

ከእንቁላሎቹ የሚፈለፈሉት ልጆች በአማካይ ሰላሳ አንድ ግራም ይመዝናሉ። በራሳቸው ኃይል የሸፈናቸውን አሸዋ ማንሳት አይችሉም። ነገር ግን እርስ በርስ በመረዳዳት እና አብረው በመስራት ወደ ውጭ መውጣት ይችላሉ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ መሬት ብቅ ይላሉ።

ኑ! ወደ ባህሩ እንሂድ!

በአሸዋ ላይ መጓዝ በእውነቱ በጣም ከባድ ነው።

ዋው! እያንሸራተተን ነው። ኑ! ቀጥታ ወደ ባህሩ እንሂድ።

ለመራባት ወደዚህ የባህርዳርቻ ከ ሃያ አምስት ዓመታት በኋላ እንመጣለን እሺ!

እስኪ አሁን እራሳችንን ስለነዚህ ትናንሽ እንሰሳት ጥቂት ጥያቄዎችን እንጠይቅ፡- እነዚህ አዲስ የተወለዱ ሕፃናት አፈሩን ከላያቸው ላይ በማንሳት ወደ ውጭ መውጣት እንዳለባቸው እንዴት አወቁ?

እንዴት ሁሉም አይተውት የማያውቁትን የባህር አቅጣጫ ሊያውቁ ቻሉ?

ምናልባት እነዚህ ትናንሽ ፍጥረታት እነዚህን ስራዎች በራሳቸው ብልሀት እንደማይሠሩት አስተውለው ሊሆን ይችላል።

ታዲያ ይህ ማሰብ የሚጠይቅ ተግባር ከየት መጣ?

ለዚህ ጥያቄ አንድ መልስ ብቻ ነው ያለው፡- አላህ ነው እነዚህን ሕሊናዊ ፀባዮች በባህር ኤሊዎች ላይ ያሳደረባቸው፡፡

## <u>የባህር ውስጥ የቅጠል ትሎች</u>

የባህር ውስጥ የቅጥል ትሎች የባህር ውስጥ ዛጎል አይነት ናቸው፡፡

አስደሳች ቅረፅ እና ደማቅ ከለር አላቸው፡፡

እንዲሁም ለስላሳ አካል አላቸው፡፡ ሆኖም የሚጠብቃቸው ሽፋን የላቸውም፡፡

ታዲያ እነዚህ ፍጥረታት እራሳቸውን እንዴት ከአዳኞች ይጠብቃሉ?

ለከለራቸው ምስጋና ይግባው የባህር ውስጥ የቅጠል ትሎች አስደናቂ መልክ ለጠላቶቻቸው እጅግ በጣም አደገኛ መርዛማነት እንዳላቸው ያሳውቃቸዋል፡፡

በዚህም ምክንያት አዳኙ እነርሱን መብላት መሞከሩን ያቆማል፡፡

አላህ ሁሉንም ፍጥረታት በተለያዩ ከለሮች እና ባህርያት ፈጥሯል፡፡ የባህር ውስጥ የቅጠል ትሎች የዚህ አንዱ ምሳሌ ናቸው፡፡

ይህ በፍጥረት መሀል ያለ ልዩነት ገደብ የለሽ የሆነው የአላህን ሀይል እና ጥበብ ያሳየናል፡፡

## ጊንጥ አሳዎች እንዴት እራሳቸውን ያመሳስላሉ?

እንዴት ናችሁ!...

ማን እንደሆንኩ አታውቁም? ጊንጥ አሳ ነኝ፡፡

በትሮፒካል አካባቢ በባህር ወለል ላይ እኖራለሁ፡፡ ወደ ባህሩ ወደላይ በፍፁም አልወጣም፡፡

ከጠላቶቼ በደረቶቼ ላይ ባሉት መርዛማ እሾሆች እጠበቃለሁ፡፡

እኔ እና የምኖርበት ኮራል ደማቅ ከለር ነው ያለን። ይህም ማለት ኮራል ውስጥ መጥፋት እችላለሁ።

ከዚህም በተጨማሪ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚደበቁ በርካታ ጓደኞች አሉኝ።

አዎ! ይህኛው ጊንጥ አሳ እንዳለው በባህር ውስጥ ፍጥረታትን ከአካባቢያቸው ነጥሎ ማየት እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው።

መኖራቸውን የምትለዩት ሲንቀሳቀሱ ብቻ ነው።

ግን ይህ ሰላማዊ ግንኙነት ከየት መጣ?

ማነው የአሳውን አካል ከአካባቢው ጋር ያመሳሰለው። እንዲሁም ተመሳሳይ ቅርፅን የሰጠው ማነው?

ስለ ከለር ፅንስ ሀሳብ ተረድቶ ከለሩን እንዲቀይር የሚያስችል ስርዓት መስራት ለአሳውም ሆነ ለሌላ ሕይወት ያለው ነገር የማይቻል ነው።

በርግጥም እነዚህን ስርአቶች የሰራ እና ሕይወት ባላቸው ነገሮች ውስጥ ያስቀመጠ ኃይል አለ።

ኃይሉ ሁሉንም ነገሮች የፈጠረው አላህ ነው።

አላህ (ሱ.ወ) ሁሉንም ፍጥረታት ከያዙት ባህሪይ ጋር ፈጥሯል።

ይህ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል።

**"ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። ከርሱ በቀር አምላክ የለም። ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው..." (ሱረቱል አንአም፡ 102)**

## <u>ሳቂታ ዶልፊኖች</u>

ዶልፊኖች ከሰው ልጅ ጋር መወዳጀት የሚችሉ አስደሳች እና ተግባቢ ፍጥረታት ናቸው።

አላህ (ሡ.ወ) ለዶልፊኖች የሰጠውን ጓደኝነት እና ታዛዥነት ከፊቶቻቸው ላይ መረዳት ትችላላችሁ።

ጓደኞቻችን ዶልፊኖች እኛ እንደምንተነፍሰው ነው የሚተነፍሱት፡፡

ሆኖም የአፍንጫ ቀዳዳዎቻቸው በጭንቅላታቸው ላይ ነው የሚገኙት፡፡

ወደ ውሀ ውስጥ ከመጥለቃቸው በፊት ዶልፊኖች በቅድሚያ አየርን ወደ ውስጥ ያስገባሉ፡፡

በመቀጠል ትንፋሻቸውን በመያዝ ወደ ውሀ ውሰጥ ይገባሉ፡፡

ወደላይ ሲወጡ በሳንባቸው ውስጥ ያለውን ትንፋሽ ይለቁታል፡፡

የሚንሸራተቱ በሚመስል ሁኔታ ውሀ ውስጥ ይዋኛሉ፡፡ ከጀልባዎችም ጋር ይወዳደራሉ፡፡

በብቁ ሁኔታ የሚዋኙበት ዋነኛ ምክንያት አላህ ቆዳቸውን በጣም ለስላሳ እና አንሸራታች አድርጎ ስለፈጠረው ነው፡፡

ይህም ውሀ ውስጥ እንዲያሳብሩ እና በፍጥነት እንዲዋኙ አስችሏቸዋል፡፡

ሌላኛው በፍጥነት እንዲዋኙ ያስቻላቸው የአፍንጫቸው አፈጣጠር ነው፡፡ የዶልፊን አፍንጮች በውሀ ውስጥ እንዲያቆራርጡ በተመቸ መልኩ ነው የተፈጠሩት፡፡

የሰው ልጆች ይህን በማጤን የጀልባን የተወሰነ ክፍል  ዶልፊኖችን በማመሳሰል ሰሩ፡፡ ይህ ጀልባዎች በፍጥነት እንዲጓዙ ያደርጋቸዋል፡፡

አላህ ለዶልፊኖች የሰላ የማዳመጥ ችሎታንም ሰጥቷቸዋል፡፡ ለዚህ የላቀ ችሎታ ምስጋና ይግባው ዶልፊኖች በብዙ ኪሎ ሜትሮች ከራቀ ቦታ የሚመጣ ድምፅን በቀላሉ መስማት ይችላሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአካላቸው ላይ ለሚገኘው ልዩ ስርዓት ምስጋና ይግባው፡፡ ዶልፊኖች በቀላሉ መንገዳቸውን በማግኘት የታዳኛቸውን ቦታ መወሰን ይችላሉ፡፡

ይህ ልዩ አቅጣጫ መጠቆሚያ ስርዓት በድምፅ ሞገዶች አማካኝነት ይሠራል፡፡ ዶልፊኖች ልንሰማቸው የማንችላቸው ድምጾችን ያወጣሉ፡፡ እነዚህ በውሀ ውስጥ ሞገድ በመሆን ይሠራጫሉ፡፡

እነዚህ የድምፅ ሞገዶች እንቅፋት ካጋጠማቸው መተወት ነጥረው ይመለሳሉ፡፡ ድምፁ እንቅፋቱን መቶት በሚመለስበት ጊዜ ዶልፊኑን የእንቅፋቱ ርቀት ምን ያህል እንደሆነ ያሳውቀዋል፡፡

የሰው ልጆች ይህን በዶልፊኑ ውስጥ ያለን ስርዓት በማስመሰል እጅግ የሰላ ሶናር በመባል የሚታወቅ አቅጣጫ መጠቆሚያ መሳሪያን ሰርተዋል፡፡

ሶናር በዋናነት በሰርጓጅ መርከቦች አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ለሶናር ምስጋና ይግባው ሰርጓጅ መርከቦች  በባህር ውስጥ ድቅድቅ ጨለማ መጓዝ ችለዋል፡፡

በርግጥም የሰው ልጅ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሰራውን ሶናር ዶልፊኖች በራሳቸው ሊሠሩት አይችሉም፡፡

ይህ በድጋሚ አላህ (ሱ.ወ) ዶልፊኖችን ከያዙት ባህሪያት ጋር እንደፈጠረ ያሳያል፡፡

## <u>አሳ ነባሪዎች</u>

አሳነባሪዎች በባህር ውስጥ ከሚኖሩ እንስሳት በሙሉ ትላልቆች ናቸው፡፡ ሰማያዊው አሳነባሪ የሚባለው የአሳነባሪ ዝርያ ሰላሳ ሜትር ወይም አንድ መቶ  ጫማ ርዝመት አለው፡፡ እንዲሁም በአማካይ ሰላሳ ቶን ይመዝናል፡፡

የሰማያዊ አሳ ነባሪ አስደናቂ ባህርይ ምንም እንኳን ግዙፍ አካል ቢኖረውም እስከ አንድ መቶ ሜትር ጥልቀት በፍጥነት መጥለቅ መቻሉ ነው፡፡ እንዲሁም ወደ ላይ ከአስራ አምስት እስከ ሀያ ሰከንድ ባለው ጊዜ ውስጥ በፍጥነት መመለሱ ነው፡፡

አላህ ላሳደረበት ልዩ አፈጣጠር ምስጋና ይግባው አሳነባሪው ያለውን ከፍተኛ ግፊት መቋቋም ይችላል፡፡የሰማያዊአሳነባሪ አጥንቶች ስፖንጅ ከመሰለ ንጥረነገር ነው የተፈጠሩት፡፡ በውሰጣቸው ያለው ባዶ ቦታም በስብ የተሞላ ነው፡፡በዚህ አስደናቂ አፈጣጠር ምክንያት የአሳው አካል እጅግ በጣም ተለማጭ እና ጠንካራ ሆኗል፡፡

ሌላኛው የአሳነባሪው ገፅታ በደም ዝውውሩ ስር ይገኛል፡፡ አሳነባሪው ለረጅም ጊዜ ሳይተነፍስ ውሀ ውስጥ ስለሚቆይ የደም ዝውውሩ ኦክስጅንን በቁጠባ እንዲጠቀም ያመቻቸዋል፡፡ አእምሮ እጅግ በጣም ኦክስጅን የሚያስፈልገው አካል ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አሳ ነባሪው ከመሬት

በታች ለረጅም ጊዜ ሲቆይ የደም ዝውውር ስርአቱ ኦክስጅን ወደሌላው አካል ላይ እንዳይሄድ በመቀነስ አእምሮው ላይ ያጠራቅመዋል፡፡

ይህም አሳነባሪው በባህሩ ውስጥ ሳይተነፍስ ከአስራ አምስት እስከ ሀያ ደቂቃዎች እንዲቆይ ያስችለዋል፡፡

ይህ ሳይንቲስቶችን ያስደመመ አስደናቂ ስርዓት ሌላኛው የአላህ የመፍጠር ጥበብ ምሳሌ ነው፡፡

ሁላችሁም በጭንቅላቱ ላይ ስላለው ቀዳዳ ታውቃላችሁ፡፡ አሳነባሪው ውሀን ያፈናጥቅበታል፡፡ ይህ የእንስሳው አፍንጫ መሆኑን ታውቃላችሁ?

ብዙ ሰዎች አሳው  ከዚህ ቀዳዳ ውሀ የሚያፈናጥቅ ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም፡፡ አየርን ነው ከሳንባው የሚያወጣው፡፡

ይህ አየር በውሀ ትነት የተሞላ እና ከአካባቢው አየር የበለጠ ሙቅ ስለሆነ ከሩቅ ሲታይ አሳነባሪው ውሀ የሚረጭ ይመስላል፡፡

ብዙ ሰዎች ከሚያስቡት በተቃራኒው አሳነባሪዎች የባህር ውሀን አይጠጡም፡፡ ጨዋማ ውሀን መጠጣት ሕይወት ላላቸው ነገሮች ጎጂ ነው፡፡ ስለዚህ የሚፈልጉትን ውሀ ከሚመገቡት ምግብ ያገኛሉ፡፡

አሳነባሪዎች በጣም የሰላ የመዳሰስ እና የመስማት ስሜት አላቸው፡፡ ልክ እንደዶልፊኖች አሳ ነባሪዎችም የተለያዩ ድምፆችን ውሀ ውስጥ በማውጣት ተመልሰው ከሚመጡት የገደል ማሚቱዎች አቅጣጫቸውን ይለያሉ፡፡

ሳይንቲስቶች እነዚህ ከአሳነባሪዎች የሚወጡት ድምፆች እጅግ ውስብስብ የሆኑ ቋንቋዎች እንደሆኑ ያስባሉ፡፡ ይህ ቋንቋ አሳነባሪዎችን በማገናኘት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

## ሲሎች

አብዛኛዎቻችን በቴሌቪዥን እና ሰርከሶች ላይ የምናውቃቸው ሴሎች አብዛኛውን የሕይወታቸው ክፍል ውሀ ውስጥ ያሳልፋሉ፡፡

ሲሎች የተዋጣላቸው ዋናነተኞች እና ባህር ጠላቂዎች ናቸው፡፡

እኛ መሬት ላይ እንደሚመቸን ሁሉ እነሱም በባህር ውስጥ እና በበረዶ ላይ ይመቻቸዋል፡፡

በፀደይ ወራት እንኳን እነሱ የሚኖሩበት አካባቢ የሙቀት መጠን ከዜሮ በታች ከአምስት ዲግሪ ሴንቲግሬድ ወይም ከሀያ ሦስት ዲግሪ ፍራናይት አይበልጥም፡፡ በዚህ ቅዝቃዜ ወደ በረዶነት እንዳንለወጥ በርካታ ጥንቃቄዎችን መውሰድ እና ብዙ ልብሶችን መደራረብ አለብን፡፡ ነገር ግን እነሱ የቅዝቃዜ ስሜት አይሰማቸውም፡፡ ምክንያቱም ፀጉራቸው እና ያጠራቀሙት ስብ ከቅዝቃዜው ይጠብቃቸዋል፡፡

ሲሎች ለብዙ ይኖራሉ፡፡

ታዲያ  እናት ሲል በዚህ የእንስሳት ስብስብ ልጇን እንዴት መለየት የምትችል ይመስላችኋል?

በቀላሉ…

ልጇን ከወለደችው በኋላ እናትዬው የልጇን ሽታ የምትለይበትን የእንኳን ደህና መጣህ መሳምን ስለምትስመው ከሌሎች ቡችላዎች ጋር አይደባለቅባትም፡፡

ቡችሎች የሕፃናት ስብ በሚባል የስብ ሽፋን የተሸፈኑ ናቸው፡፡ ይህ ትንሹ አካላቸውን ሁልጊዜም ሙቅ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ልክ እንደ ሲሎች አላህ (ሡ.ወ) ሁሉንም ፍጥረታት ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር በተመቻቸ መልኩ ፈጥሯቸዋል፡፡ ይህም አላህ ምን ያህል አዛኝ እንደሆነ ያሳያል፡፡

*<u>መደምደሚያ</u>*

አሁን ስለተመለከትናቸው እንስሳት እና ስለአፈጣጠራቸው ተዐምር መለስ ብለን እናስብ…

አፅጂው አሳ፣ ክላውን አሳ፣ የባህር ውሰጥ የቅጠል ትሎች፣ ሳቂታ ዶልፊኖች፣ አሳ ነባሪዎች፣ ተወዳጅ ሲሎች…

ሁሉም አላህ (ሱ.ወ) ባህር ውስጥ የፈጠራቸው ተአምራት ናቸው፡፡ ስለ ሁሉም ነገሮች በማስተንተን እነሱንና በተፈጥሮ ውስጥ ያሉ የሕይወት አይነቶችን ስለፈጠረው አላህ ትልቅነት የበለጠ መረዳት የእያንዳንዱ አስተዋይ ሰው ኃላፊነት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በጥልቅ እንድናስተነትን በቁርአን ላይ ያዘናል፡፡

“እናንተንም በመፍጠር ከተንቀሳቃሽም (በምድር ላይ ) የሚበትነውን ሁሉ (በመፈጠሩ) ለሚያረጋግጡ ሕዝቦች ተአምራቶች አሉ፡፡” (ሱረቱል ጃሲያ:4)